የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፯
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 17
ADDIS ABABA 26th December 2012

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፮/፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ለጌዶ - ለምለም በረሃ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..............ገጽ ፮ሺ፯፻፳፪**

**CONTENTS**

**Proclamation No. 776/2012**

**Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement for Financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project Ratification Proclamation ....... Page 6722**

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፮/፪ሺ፭**

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለጌዶ - ለምለም በረሀ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፲ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አሥር ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.አ.አ ጁን ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፩ በሊዝበን የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታኅሣሥ ፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

**PROCLAMATION No. 776/2012.**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND ARAB BANK FOR ECONOMIC DEVELOPMENT IN AFRICA**

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa stipulating that the Arab Bank for Economic Development in Africa provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of USD 10,000,000 (ten million United States Dollars) for financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project, was signed in Lisbon on the 14th day of June, 2011;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 18th day of December, 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

## ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለጌዶ - ለምለም በረሃ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፮/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪. የስምምነቱ መፅደቅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአረብ ባንክ ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ጁን ፲፬ ቀን ፪ሺ፲፩ በሊዝበን የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር (አሥር ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Arab Bank for Economic Development in Africa Loan Agreement Financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project Ratification Proclamation No. 776/2012".

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Arab Bank for Economic Development in Africa on the 14th day of June, 2011 in Lisbon is herby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of USD 10,000,000 (ten million United States Dollars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት